# SY25-26 እና SY26-27 Columbia Heights የትምህርት ካምፓስ (CHEC) የቅበላ መስፈርቶች መመሪያ

ለክፍል፡ 9-12

**ማስታወሻ፥** ይህ መመርያ ለSY25-26 እና SY26-27 የተማሪ ቅበላ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**Columbia Heights የትምህርት ካምፓስ የቅበላ መስፈርቶች፥** Columbia Heights Education Campus (CHEC) ውስጥ ለዕድሜ ዘመን ትምህርት ትጉ የሆኑ፣ ለማህበረሰቡ አንዳች አስተዋጽኦ የማበርከት ፍላጎት ያላቸውን እና የማህበራዊ ፍትህ ጥማት ያላቸውን ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ እና የእውቀት ፍላጎት ያላቸውን ምሁራን ማፍራት እንፈልጋለን። በጣም ስኬታማ የሆኑት አመልካቾች የእድገት አስተሳሰብ ያላቸው እና የልቀት እና የፈጠራ ቋሚ ትሩፋት ያላቸው ሆነው አግኝተናቸዋል።

**የ CHEC የቅበላ ሂደት፥** የኛ የተማሪ ቅበላ ሂደት የፍላጎት የዳሰሳ ጥናቶችን፣ ሁለት (2) የመምህር የድጋፍ ደብዳቤዎችን እና የውጤት መግለጫ ካርድ ግምገማን ያካትታል፤ ሁሉም በMy School DC አጣ መተግበርያ መቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም አመልካቹ በቃለ መጠይቅ ላይ እንዲሳተፍ ተጠይቋል። የትኛውም አንድ የቅበላ መስፈርት ወይም ክፍል ብቃትን ለመወሰን ብቸኛ መለኪያ አይሆንም።

<u>በአሁኑ ወቅት የCHEC የ 8ኛ ክፍል ተማሪ ለሆኑ አመልካቾች</u>

CHEC ከ6-8ኛ ክፍል የተጎራባች እና የፕሮግራም መጋቢ ለሆኑት እና ከ9-12ኛ ክፍል ለተመራጭ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እድል ይሰጣል።

**8ኛ ክፍልን በCHEC ያጠናቀቁ ሁሉም አመልካቾች My School DC ማመልከቻ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው ለ 9ኛ ክፍል ትምህርት CHEC የመመዝገብ መብት አላቸው።**

እያንዳንዱ የማመልከቻ ሂደቱ ክፍል ውጤት የሚሰጠው ሲሆን ከታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ይመዘናል። አነስተኛውን 70/100 አጠቃላይ ውጤት ያመጡ አመልካቾች በሙሉ ለቅበላ ብቁ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሲሆን ባለው ፍላጎት እና ቦታ በመኖሩ ላይ በመመስረት አጠቃላይ ውጤታቸው ከ70 በታች የሆነ ተጨማሪ አመልካቾች ለቅበላ ብቁ ናቸው ተብሎ ሊወሰን ይችላል። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።

| የቅበላ ክፍል | ክብደት | ማሳሰቢያዎች |
|---|---|---|
| የሪፖርት ካርድ ግምገማ (GPA እና ተሳትፎን ይጨምራል) | 30/100 ነጥብ | CHEC እንደ የሪፖርት ካርድ ግምገማ አንድ አካል ሆኖ የትምህርት ውጤቶችን እና ተሳትፎን ይገመግማል። ሁሉም አመልካቾች የዚህን ዓመት የመጀመርያ ሩብ አመት የውጤት መግለጫ ካርድ እና የባለፈውን ዓመት የመጨረሻ ካርዳቸውን እንዲያቀርቡ ተጠይቀዋል። የተጠየቀ አነስተኛ አማካይ ወይም የአቴንዳንስ መጣኔ የለም፣ ነገር ግን ማመልከቻው የተሟላ ነው እንዲባል እና ለቅበላ ታሳቢ ለመደረግ የውጤት መግለጫ ካርድ ከማመልካቸው ጋር የግድ መቅረብ አለበት።<br><br>በዋናነት በCHEC ስኬታማ ለመሆን የተዘጋጁ አመልካቾች 2.5 GPA ወይም ከዚያ በላይ እና 90 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የአቴንዳንስ መጣኔ አላቸው።<br><br>ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል፣ አመልካቾች በቂ ክሬዲት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ህጋዊ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትራንስክሪፕታቸውን ማቅረብ ያለባቸው መሆኑን እና በወቅቱ እስኪመረቁ ድረስ ክትትል የሚደረግ መሆኑን እባክዎ ልብ ይበሉ፣ ምክንያቱም CHEC የሚፈቅደው 28 Carnegie ምእራፎችን ነው። |

| | | |
|---|---|---|
| ቃለ መጠይቅ | 25/100 ነጥብ | CHEC ለትምህርት፣ ለቋንቋ እና እኩልነት ጥልቅ ፍላጎት፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት ቁርጠኝነት ያላቸውን እና ለማህበራዊ ፍትህ ባላቸው ጥማት ረገድ ያላቸውን ትጋት እና ጥንካሬ በተግባር ማሳየት የሚችሉ አመልካቾችን በመለየት አጥብቆ ያምናል። በተማሪው የትምህርት ፍላጎት እና ችሎታዎች ላይ ግልጽ የሆነ ፍንጭ ለማግኘት፣ የማለፍ እድሉ ያላቸው አመልካቾች ብቻ በማመልከቻ ሂደቱ የቃለ መጠይቅ ክፍል ላይ እንዲሳተፉ እንጠይቃለን።<br><br>በቃለ መጠይቁ ወቅት፣ CHEC የሚፈልገው የማለፍ እድል ያላቸውን ተማሪዎች ስብዕና፣ ፍላጎቶች፣ እሴቶች እና መነሳሻዎች ለይቶ ማወቅ እንዲሁም ስለተማሪው ቤተሰብ እና የቤት ሕይወት እውቀት ማግኘት ነው። በመጨረሻ ተማሪው ወደ ትምህርት ክፍሉ የሚያመጣቸው ክህሎቶች ምን ምን እንደሆኑ ይወስናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።<br><br>በጤና መመሪያ እና በቤተሰብ ሁኔታዎች ምክንያቶች፣ ለ SY25-26 ቃለመጠይቆች በኦንላይን ሊደረጉ ይችላሉ። |
| የፍላጎት የዳሰሳ ጥናቶች | 15/100 ነጥብ (የማጠናቀቂያ ውጤት ብቻ የተሰጠው) | የፍላጎት ዳሰሳ ጥናቶቹ በMy School DC ማመልከቻ የገቢ ሲሆን ውጤቶች የተሰጡት በመቅረባቸው/በመሞላታቸው ላይ ብቻ በመመስረት ነው። ሁሉም አመልካቾች የMy School DC እጣ ማመልከቻ አንድ አካል አድርገው ይህን ክፍል የግድ ማሟት አለባቸው።<br><br>የዳሰሳ ጥናቶቹ ጥቅም ላይ የዋሉት እድሉ ባለው ተማሪ ላይ፣ ከትምህርት ቤት ልምዳቸው ምን አገኛለሁ ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ እና ወደ ትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ምን ማምጣት እንደሚችሉ ፍንጭ ለማግኘት ነው። በተጨማሪም የፍላጎት የዳሰሳ ጥናቶቹ እድሉ ያለውን ተማሪ ፕሮግራም ውስጥ ለማስገባት እና የትምህርት ተሳትፎን/ምደባን ለመወሰን ያግዛሉ። |
| የድጋፍ ደብዳቤዎች | 30/100 ነጥብ | CHEC እድሉ ያለው ተማሪ በትምህርት ቤት ስላለው ልምድ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እና ለውጤት መግለጫ ካርዳቸው አውድ ለመስጠት የድጋፍ ደብዳቤዎችን ይጠቀማል።<br><br>CHEC በአጠቃላይ ሁለት (2) የድጋፍ ደብዳቤ ይጠይቃል። በተጠየቀው መምህር የተሞላው አንድ ብቻ ከሆነ፣ ተማሪውን በቀረበው አንድ የድጋፍ ደብዳቤ ብቻ እንመዝነዋለን። የቀረበ የድጋፍ ደብዳቤ ከሌለ፣ ትምህርት ቤቱ ነጥቦቹን ለውጤት መግለጫ ካርድ እና ለቃለ መጠይቅ መልሶ ይበትናቸዋል።<br><br>ትምህርት ቤቱ በተቻለ መጠን ስለአመልካቹ ተጨማሪ መረጃ ማግኘቱን ለማረጋገጥ፣ አመልካቾች እና ቤተሰቦቻቸው በነሱ ስም የድጋፍ ደብዳቤ ከሚያቀርቡላቸው መምህራን ጋር ሆነው እንዲከታተሉ በጥብቅ እናበረታታቸዋለን። |
| **70 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ያገኙ አመልካቾች በሙሉ ለቅበላ ብቁ ይሆናሉ።<br>ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ ባገኙት ጠቅላላ ነጥብ መሰረት ደረጃ ይሰጣቸዋል።** | | |